# የ Ericsson አጠቃላይ አቅራቢ የሙያ ጤና እና ደህንነት መስፈርቶች

Requirement Specification

**ማውጫ**


**1** መግቢያ ... **3**

**2** ትርጓሜ ... **3**

**3** የ**OHS** አስተዳደር ስርዓት ... **4**

**4** የ**Ericsson** ብቻ የሆኑ የአቅራቢ የ**OHS** መስፈርቶች ... **7**

**5** የለውጥ መረጃ ... **7**

# 1 መግቢያ

በEricsson፣ እብረውን ለሚሰሩት ሰዎች በሙሉ የምናስብ ሲሆን፣ ሁሉም ሰው በየቀኑ ደህንነቱ ተጠብቆ ወደ ቤት መመለሱን ማረጋገጥ እንፈልጋለን። ሰራተኞቻችንን፣ የአቅራቢዎቻችን ሰራተኞችን እንዲሁም እኛን ወክሎ የሚሰራን ማንኛውንም ሰው ጨምሮ ለሁሉም ደህንነቱ የተጠበቀና ጤናማ የስራ አካባቢን ለማቅረብ በቁርጠኝነት እንሰራለን። ግባችን ዜሮ ኢላማ ነው - ዜሮ ከስራ ጋር የተዛመዱ ግድያዎች እና ጉዳቶች እና በሽታዎችን ያካተቱ ክስተቶ። ኢላማ ዜሮ በEricsson እና በአቅራቢዎቻችን መካከል ያለ የጋራ ቁርጠኝነት ነው።  ይህ ስምምነት የአቅራቢ ሠራተኞችን እና የአቅራቢ ንዑስ ስራ ተቋራጮችን ሠራተኞችን ጨምሮ በEricsson ስም በሚሰሩ በሁሉም ግለሰቦች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

Ericsson ከአስተዳደር ስርዓቶች፣ ከጸረ ሙስና እና የስራ ስነምግባር፣ ከሠብዓዊ እና የሠራተኛ መብቶች፣ ከስራ ላይ ጤና እና ደህንነት (OHS) እና ከስራ ቦታ የአካባቢ ጥበቃ አስተዳደር ጋር የተያያዙ መስፈርቶችን በመዘርዘር የስነምግባር ደንብ አውጥቶ ለሁሉም አቅራቢዎች ሰጥቷል። የEricssonን የስነ ምግባር ደንብ ለማግኘት፣ እባክዎ ይህን ድረገጽ ይጎብኙ: [http://www.ericsson.com/responsible-sourcing](http://www.ericsson.com/responsible-sourcing)

ይህ ሰነድ Ericsson በሁሉም የEricsson አቅራቢዎች ላይ ተፈጻሚ ያደረጋቸውን አስገዳጅ እና የውል አስገዳጅነት ያላቸውን የስራ ላይ ጤና እና ደህንነት (OHS) መስፈርቶችን ይዘረዝራል። በዚህ ሰነድ ውስጥ ‹‹አቅራቢ›› ወይም ‹‹የአቅራቢ ሰራተኞች›› የሚሉት ቃላት ሁሉንም የአቅራቢ ሰራተኞችን፣ ስራ ተቋራጮችን፣ ንዑስ ስራ ተቋራጮችን፣ የአቅራቢ ወኪሎችን እና ሌሎች በአቅራቢዎች ተጽዕኖ ወይም ቁጥጥር ስር ያሉ ግለሰቦችን ያጠቃልላሉ። አቅራቢው እነዚህ ሁሉም ግለሰቦች በዚህ ሰነድ ውስጥ የተገለጹትን መስፈርቶች የሚያሟሉ መሆናቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት።

Ericsson በዚህ ሰነድ ውስጥ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች አቅራቢዎች ማክበራቸው ለማረጋገጥ የመመርመር እና የመገምገም መብት አለው።

# 2 ትርጓሜ

**ከፍተኛ ተጋላጭነት ያለባቸው ተግባራት**፡- አስፈላጊዎቹ የደህንነት ጥንቃቄዎች ሳይደረጉ በመቅረታቸው በሠራተኛው ወይም በተጎዳው ሰው ላይ ለሞት ወይም ለሞት ሊዳርግ የሚችል ከፍተኛ የአካል ጉዳት ወይም ሕመምን የመከሰት እድሉ ያለበትት ተግባር ወይም ስራ ነው። እነዚህ ተግባራት በተለምዷቸው ከፍተኛ ትኩረትን፣ ጥንቃቄን ወይም ብቃትን የሚሹ አደገኛ ተግባራት ናቸው። እነዚህ እንቅስቃሴዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

- በከፍታ ላይ መውጣት እና ስራ የሚከተሉትን ያካትታሉ ግን በእነዚህ ብቻ አይወሰኑም፡-
    a. መሰላሎችን መጠቀም
    b. የአየር ላይ ማንሻዎችን መጠቀም
    c. የቁሳቁሶች/መሳሪያዎች መሳብ እና በእጅ ወይም በሜካኒካል ማንሳት
- ተሽከርካሪ መንዳት

- ○ በኤሌክትሪክ መስራት
- ○ የግንባታ እና የሲቪል ስራዎችን ማከናወን
- ○ በእጅ የሚሰሩ መሳሪያዎችን መጠቀም
- ○ ለራዲዮ ፍሪኩዌንሲ እና ኤሌክትሮማግኔቲክ ፊልዶች ተጋላጭነት
- ○ የኬሚካሎች አጠቃቀም
- ○ በቂ አየር ወደሌለበት በጣም ጠባብ ቦታ መግባት

**ክስተት፡-** ለሞት፣ ለጉዳት፣ ለህመም ወይም የመሳሪያ/ንብረት ጉዳት ያስከተለ ወይም የማስከተል አቅም ያለው ያልታቀደ ክስተት ወይም ተጋላጭነት ነው። የተጎዳው ግለሰብ በስራ ላይ እያለ፣ ከስራ ጋር የተያያዘ እንቅስቃሴን ሲያደርግ አሊያም ከስራ ጋር በተዛመደ ተግባር ሲጎዳ ይከሰታል። (ወደ ሥራ በመጓዝ እና በመመለስ ጊዜ የሚከሰተውን ክስተት ያጠቃልላል።)

**ለጥቂት መትረፍ፡-** ለሞት፣ ለአካል ጉዳት፣ ለህመም ወይም ለመሳሪያ/ንብረት ጉዳት ያላደረሰ ነገር ግን ይህን የማድረግ አቅም የነበረው ያልታቀደ ክስተት ነው።

**የስጋት ምልከታ/የአደጋ መለያ**፦ እንደ አደገኛ ዕቃ፣ ክስተቶች፣ ባህሪያት፣ ወይም የአካል ጉዳት፣ ህመም ወይም የንብረት ጉዳት ሊያስከትሉ የሚችሉ ሁኔታዎች ያሉ አደጋዎች ወይም ስጋቶች።

**ሥራ የማቆም ሥልጣን፥** እነሱ ወይም ሌሎች ለሞት፣ ለጉዳት ወይም ለአደጋ የመጋለጥ ሁኔታ ላይ ናቸው ብለው ሲያምኑ በEricsson፣ በአቅራቢ ሰራተኞች ወይም በአቅራቢ የተሰማሩ ሌሎች ሰዎችን ሥራ ማቆም ወይም በሥራ ሁኔታ ውስጥ ጣልቃ እንዳይገቡ ማድረግ።

# 3 የOHS አስተዳደር ስርዓት

አቅራቢው ቢያንስ የሚከተሉትን አላባዎች የሚያካትት አንድ የOHS አስተዳደር ስርዓት ይኖረዋል። አቅራቢው የOHS አስተዳደር ስርዓትን ለማቋቋም፣ ለማስፈጸም፣ ለማስቀጠል እና ለማሻሻል ብቃት ያላቸውን የOHS ሠራተኞችን ጨምሮ አስፈላጊ ሀብቶች መኖርም ያረጋግጣል።

- **የOHS ፖሊሲ**

  አቅራቢው የOHS ፖሊሲ ሊኖረው ይገባል። ፖሊሲው ከአቅራቢው OHS ስጋቶች ተለምዶ እና መጠን ጋር የሚጣጣም መሆን እና ጉዳትን እና ህመምን ለመከላከል ብሎም ቀጣይነት ያለው መሻሻል ለማድረግ ቁርጠኝነትን ሊያካትት ይገባል።

- **ለህጋዊ መስፈርቶች እና ለEricsson መስፈርቶች ተገዢ ስለመሆን**

  አቅራቢው ተፈጻሚ ለሆኑ ለሁሉም የOHS ህጋዊ መስፈርቶች እና ለEricsson መስፈርቶች ተገዢ ይሆናል። አቅራቢው የህግ ተገዢነትን የሚያረጋግጥበት እና በህጋዊ እና የEricsson መስፈርቶች ላይ የተደረጉ ለውጦችን የሚቆጣጠርበት አንድ የአሠራር ሂደት አለው። በህጋዊ እና የEricsson መስፈርቶች መካከል መጣረስ በሚያግጥምበት ጊዜ፣ ጠበቅ ያለው የበላይነት ይኖረዋል።

- **የስጋት ጥናት/ትንተና**

  አቅራቢው ውስጣዊ እና ውጫዊ ሁኔታዎችን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በአቅራቢው ሰራተኞች፣ በEricsson ስም በሚሰራ በማናቸውም ሰው ላይ ወይም ከስራ እንቅስቃሴ ችግር ሊደርስባቸው በሚችሉ ሌሎች ሰዎች ላይ ሊደርሱ የሚችሉ አደጋዎችን ለመከላከል ስጋት ላይ የተመሰረተ እርምጃ ይወስዳል።

  አቅራቢው በቁጥጥር የስልጣን ተዋረድ ላይ በመመስረት አደጋዎችን ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ የስጋት ትንተና ይሰራል (ማስወገድ፣ መተካት፣ የምህንድስና ቁጥጥሮች፣ አስተዳደራዊ ቁጥጥሮች፣ የግል የአደጋ መከላከያ መሳርያ)። በተጨማሪም አቅራቢው ለስራ ላይ አደጋ የመጋለጥ ከፍተኛ ስጋት ላለባቸው ለአቅራቢው ሰራተኞች እንዲሁም እንደ አካል ጉዳተኛ፣ ነፍሰ ጡር ሴቶች እና ልጅ አሳዳጊ የሆኑ/ጡት የሚያጠቡ እናቶች ለመሳሰሉ ተጋላጭ ሰራተኞች ልዩ የትበቃ እና የድጋፍ እርምጃዎችን ይወስዳል። የስጋት ትንተናዎች ከስራ እናከዋና ዋና ለውጦች በፊት የሚደረጉ ሲሆን በየጊዜው እየተሻሻሉ ወቅታዊ ይደረጋሉ።

- **የአቅራቢ ሠራተኞች ምክክር እና ተሳትፎ**

  አቅራቢው ለአቅራቢው ሠራተኞች ምክክር እና ተሳትፎ ተግባራዊ የሚሆን አንድ የአሰራር ሂደት ተግባራዊ የሚያደርግ ሲሆን ይህ የአሰራር ሂደት ካለ የሰራተኞች ተወካዮች በዝግጅት፣ እቅድ፣ አፈጻጸም፣ በአፈጻጸም ግምገማ እና በOHS አያያዝ ስርዓት ቀጣይነት ያለው ማሻሻያ እንዲሁም አደጋዎችን በመለየት፣ ስጋቶችን በመገምገም እና የቁጥጥር እርምጃዎችን በማስፈጸም ላይ ይሳተፋሉ።

- **ስልጠና እና ተወዳዳሪነት/ብቃት**

  አቅራቢው ለሁሉም የአቅራቢው ሠራተኞች ተገቢውን ስልጠና የሚሰጥ ሲሆን ስልጠናው ከስራ በፊት መወሰዱን እና ከዚያ በኋላ በየጊዜው መወሰዱን ያረጋግጣል። በነዚህ ብቻ የተወሰነ ባይሆንም፣ ስልጠናው የስራ ስጋቶችን እና ተፈጻሚ የሚደረጉትን የመቆጣጠርያ እርምጃዎች ያካትታል። ሁሉም የአቅራቢው ሰራተኞች የተመደቡባቸውን ስራዎች የማከናወን ብቃት ያላቸው መሆኑን አቅራቢው ያረጋግጣል።

  በተጨማሪም አቅራቢው ከጤና አንጻር ብቁ የሆኑ ሠራተኞች ብቻ ለስራ መሰማራታቸውን ያረጋግጣል።

- **የአሠራር ቁጥጥር**

  ማናቸውም ስራ ከመጀመሩ በፊት የሚደረገው ማጣራት እና በስራ ወቅት የሚደረገው ምርመራ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከፍተኛ ስጋት ያላቸው ስራዎች ጥብቅ ቁጥጥር ይደረግባቸዋል።

  አቅራቢው ለሰራተኞቹ ያለምንም ክፍያ የሀገር ውስጥ እና ዓለምአቀፍ መስፈርቶችን የሚያሟላ ተገቢ የግል የአደጋ መከላከያ መሳርያ (PPE) መሰጠቱን ያረጋግጣል። በተጨማሪም የአቅራቢው ሰራተኞች በPPE ትክክለኛ አጠቃቀም ላይ መመርያ እና ስልጠና ይሰጣቸዋል እንዲሁም ቁጥጥር ይደረግባቸዋል።

አቅራቢው የሚከተሉትን የEricssonን የስራ ወሰን በሚመለከት [የEricsson OHS የአሠራር ደረጃዎች]ን በሚከተሉት ዘርፎች የሟላ ወይም የተሻለ መሆን አለበት፦

- ከፍ ባሉ ቦታዎች ላይ መውጣት እና መስራት
- ማሽከርከር እና የተሽከርካሪ ደህንነት
- በኤሌክትሪክ መስራት
- የኬሚካል አጠቃቀም
- ለራዲዮ ፍሪኩዌንሲ ኤሌክትሮማግኔቲክ ፊልዶች ተጋላጭነት
- ማመሪያ አስተዳደር
- ለብቻ መስራት
- የተጣበበ ቦታ መግባት
- የግንባታና የሲቪል ስራዎች አስተዳደር
- የግል የደህንነት መከላከያ መሳሪያ
- የእሳት አደጋን መከላከያ
- የአካባቢና የስራ ላይ የድምጽ ብክለት

አቅራቢው ስምምነትላይ የተደረሰበትን የስራ ወሰን ከመጀመሩ በፊት የሚተገበሩትን የEricsson OHS አሠራር ደረጃዎችን መለየት አለበት።

Ericsson OHS የስራ መስፈርቶች በEricsson በማንኛውም ጊዜ ሊሻሻሉ ይችላሉ። ከEricsson ጋር በጽሑፍ የተለየ ስምምነት ካልተደረገ በስተቀር የተለቀቁት ውል ከመፈራረማቸው በፊትም ሆነ በኋላ ምንም ይሁን ምን የEricsson OHS የአሠራር ደረጃዎች ማሻሻያዎች ከተለቀቁበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናሉ። (Ericsson ማናቸውንም ማሻሻያዎችን ለአቅራቢው ያስተላልፋል።) አቅራቢው የሚመለከተውን የሥራ ወሰን ለማቅረብ ባለው አቅም ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድር በEricsson OHS አሠራር ደረጃዎች ላይ ለውጥ እንዳሉ በሚያውቅበት ወቅት፣ Ericsson እና አቅራቢው ለውጡን ተግባራዊ ለማድረግ በሚቻልበት ዘዴ፣ አንድምታ እና የጊዜ ሰሌዳ ተወያይተው ይስማማሉ።

- **የአደጋ/ድንገተኛ ጊዜ ዝግጁነት እና ምላሽ**

አቅራቢው አግባብነት ያላቸውን የአደጋ ጊዜ እቅዶች በማውጣትና ተፈጻሚ በማድረግ ሊከሰቱ የሚችሉ የአደጋ ሁኔታዎችን ይለያል እንዲሁም ለነዚህ ሁኔታዎች እንዴት ምላሽ እንደሚሰጥ ያውቃል። የአደጋ ጊዜ እቅዶች ለሚመለከታቸው የአቅራቢ ሠራተኞች ይገለጻሉ። የአደጋ ጊዜ ተግባራት አግባብነት ባላቸው ህጋዊ መስፈርቶች መሰረት የሚፈጸሙ መሆን አለባቸው። የዚህ አይነት መስፈርቶች ከሌሉ፣ ቢያንስ በአመት አንድ ጊዜ ይከናወናሉ።

- **አደጋን ሪፖርት ስለማድረግና ቁጥጥር**

አቅራቢው የተከሰቱ አደጋዎችን ሪፖርት ለማድረግ እና ለመመርመር እና የእርምት እርምጃዎችን ለመውሰድ አንድ የአደጋ አያያዝ ስርዓት ይዘረጋል፣ ያስፈጽማል እንዲሁም ተፈጻሚነቱን ያስቀጥላል።

አቅራቢው ሁሉም የአቅራቢ ሰራተኞች የደረሱ ጉዳጦችን፣ የመቁሰል አደጋዎችን፣ ህመሞችን፣ አደጋዎችን፣ስጋቶችን እንዲሁም የሰራ ማስቆም ባለስልጣን ጉዳዮችን ጨምሮ የOHS አደጋዎችን ሪፖርት እንዲያደርጉ ያበረታታል።

ከEricsson ጋር የተያያዙ አደጋዎች መሰረታዊ መንስዔያቸውን ለመከላከል እና ዳግም እንዳይከሰቱ ለመከላከል ለEricsson ሪፖርት መደረጋቸው አቅራቢው የማረጋገጥ ሃላፊነት አለበት። የEricsson ዓለም አቀፍ የአደጋ ሪፖርት ማቅረቢያ መሳሪያ (GIRT) የOHS አደጋዎች ሪፖርት የሚደረጉበት መሳሪያ ነው።

በስራ ላይ የደረሰ የመቁሰል አደጋ ወይም በሽታ/ህመም የደረሰባቸውን የአቅራቢውን ሰራተኞች ወደስራ መመለስ የሚያመቻች ሂደት ተግባራዊ ይደረጋል።

ስራ የማስቆም ባለስልጣንን የሚመለከት ዝርዝር መረጃ ለማግኘት እባክዎ የአቅራቢዎችን የስራ ማስቆም ባለስልጣን ሂደት ይመልከቱ።

- **የአፈጻጸም መለኪያ እና የማሻሻያ ፕሮግራም**

  አቅራቢው የOHS አያያዝ ስርዓቱን ይገመግማል፣ የOHS አፈጻጸሙን ይለካል እንዲሁም ዓላማዎችን እና የስራ እቅዶችን ጨምሮ የOHS ማሻሻያ ፕሮግራም ተፈጻሚ ያደርጋል።

አቅራቢው አግባብነት ያላቸው ሰነዶች ወቅታዊ መደረጋቸውን እና ምዝገባዎች መያዛቸውን ያረጋግጣል።

# 4 የEricsson ብቻ የሆኑ የአቅራቢ የOHS መስፈርቶች

የEricsson ብቻ የሆኑ የአቅራቢ የOHS መስፈርቶች አገልግሎቱን ለEricsson በሚሰጥበት ጊዜ ከፍተኛ ስጋት ያለባቸውን ተግባራት በሚያከናውነው አቅራቢ ላይ አስገዳጅ ናቸው። በሌሎች አቅራቢዎች ሁሉ ተፈጻሚ እንዲደረጉ ይመከራሉ።

የEricsson ብቻ የሆኑ የአቅራቢ የOHS መስፈርቶች በEricsson የአቅራቢ OHS መስፈርቶች ገጽ ላይ ሊገኙ ይችላሉ።

# 5 የለውጥ መረጃ

ከመጨረሻው ክለሳ በኋላ የተደረጉ ለውጦች፥

- ወቅታዊ የተደረገ ሰነድ መዋቅር
- ከቀድሞው እትም የተወሰዱ በተጨማሪ የተጠቀሱ መስፈርቶች
- አዳዲስ መስፈርቶችን አካቷል (ማለትም የአቅራቢ ሠራተኞች ምክክርና ተሳትፎ፣ የስራ ቁጥጥር እና የአደጋ ዝግጁነት እና ምላሽ)


© Ericsson AB 2025